ከጎቦ ዉቃው ጥቅምት 6 2000

## <u>አሃዱ፤ክለቱ፤ሰለስቱ</u>

አሃዱ. . .ክለቱ. . . ሰለስቱ
ነጋ፤መዋ፤ፅጌ፤. . . ቅባት ከ"ልደቱ"
በአንድ ወሰለቱ፤. . .ለጥፋት በረቱ
በአንድ ወሰለቱ፤. . .በህዝብ ተዛበቱ
. . . እነ ተንኮል ቕቱ
"ሳይቃጠል በቅጠል" ነበረ ተረቱ
ያኔ ብንቀጣው. . .ሲውል ከ"ልደቱ"
አይደግመውም ነበር. . .ሾተላይነቱ
ፋይዳ የለሽ ገልቱ. . .አሾክሹአኪነቱ

ይህ የጠዋት. . .ልክፍቱ
የስልጣን-ጥም. . .መሰረቱ
ከመለስ-በረከት. . .መጣባቱ
ትክሻው ላይ የጣለው. . .
. . .የቃፊርነት ቡቱቱ
አለቀለት፤ነተበ. . .
. . .አያስጥለው ከውርደቱ።

አዳሩ ከ"አፄ" ቤት. . .
. . .ውሎው ከ እኛ ጋራ
. . .እኛኑ ሰይሞ "ፋራ"
የሞነጨረው አቡአራ
በራሱ ላይ ቤት ሰራ
ዳግም ላያንሰራራ
"ነጋ" አውቅልሃለሁ ብሎ ሲደነፋ
. . .ተንኮሉ ከፍቶ ሲከረፋ
ሃቅ የሚነግር አይጥፋ!
<u>"መስፍኔ" አረገው ይፋ!</u>

ከቦ ዉቃው

“የነፃነት-ጎህ” ገበያ
የተንኮሉ መንደርደሪያ
ጉቦ ኖሮአል መታያ!
የኔን ቢጤ ማታለያ
ወደ አፄው ቤት መግቢያ
ወደ ስልጣን መንጠልጠያ
የትግሉን አከርካሪት. . .
. . .ለዘለአለም መስበሪያ
. . .ወያኔ ሰራሽ ዛቢያ
ወይ ሙያ! ወይ ሙያ!
ድንቄም ሙያ! ድንቄም ሙያ!

ላም አለኝ በሰማይ
ነጋም ዋይ! ፅጌም ዋይ! መዋም ዋይ!
ህዝብ እና አገር ሽጦ. . .
. . .ለመውጣት ወደ ላይ።

ገናም ከጠዋቱ. . .

በአሲምባ ኮሪደር
አድዋ ሲንደረደር
አድዋ ሲደራደር
ቅስናውን ወስዶ. . .
. . .በጋዳሪፍ ሲበር
ከቶ ያቅበታል. . .
. . .በአ-ገኘው ማደር
. . .ለአ-ገኘው ማደር
. . .መሸጥ ህዝብ ና አገር
መሸ ዶክተር!. . .”ነጋ ዶክተር!።
በጁ በእግሩ ቢውተረተር
ቢያውገረግር. . .ቢያደናብር
መድሀኒት አይሆን ላገር

በሬት የተለወሰው ማር
ኸረ እዚያው ይሙት!ይቀበር!

ግና
ደም-ስጋ ሳይገነፋ
. . .ስልጣን በቀፈፋ
ከፈረንጆች በዳረጎት
ይገኝ ይሆን አርነት??

አረ የጉድ አገር! አይሰማ የለ!
ብቅሉም መዘነ. . .
. . .ስካሩም አየለ
ባተሌው ወገኔ እየተደለለ
ቆመጠጠ ጠላው. . .
. . .እሬት እሬት አለ
ምነው ብንራመድ እየተስተዋለ።

ትንንስ ጭራቆች. . .እበቱ ወለደ
ደግሞ ከወደታች “ዳዊቱ አበደ”
ደግሞ ከወደታች “ዳዊቱ ከበደ”
እንዳጨበጨበ፤ እንደመለገደ
ዓለም-ዓቀፍ ብሎ. . .
የማያቅበትን፤ልቡ እንዳበጠ
ሙሴነትም ቃጣው. . .
ዓለም-ዓቀፍ ብሎ፤አደባ፤አደፈጠ
ደርሶ. . .
ይሂማ ባተሌ ለስልጣን ቋመጠ
ግን አያገኛትም ቀረ እንዳጋጠጠ።

ይልቁንማ!. . .እንደኔማ!
ይልቁንማ!. . .እንደማማ!
. . .አገር ያስቀድሚል እንጅ!

. . .አርነት ይኗል እንጅ!
. . .እጅ ሰጥቶ ለፈረንጅ
ጦርን መስበቅ በወዳጅ
የሞት ሞት እንግዲህ ነው. . .
. . .እውነት ካለ ፈራጅ።

አሁንማ!
“ሃይል! የእግዚአብሄር ነው. . .
“ሃይሉን” ይዘን መምዘግዘግ ነው
እንበል አስራሁለት እንበል
“ብርቱካንም” አትማለል
እንበል አስራሁለት እንበል
“ብርቱካንም” አትታልል
ተዋረዱን ትከተል!
“ሃይሉ” መዝለቂያ ይሆናል፤
የእምነት፤የታሪክ ባለወል
ያገር ተስፋ! የጀግና አምሳል
ራእያችንን ሰንቋል
ድርብ ፀዳል፤ድርብ ፀዳል
መንገዱም ግልጽ ሆኖአል።

ቸር ይግጠመን

ነበልባል